# ኢሕአፓ

በዚህች የመስቅ ዓለም
የድሆች መጠለም
ግፏን ተገፍቶ እየደማ ልቤ
የህዝብ ጥያቄ ትግል አነግቤ
ህመማቸውን ስታመም
እንግልታቸውን ስከላተም
ርሃባቸውን ተርቤ
በደላቸውን ደርቤ
እርዛታቸውን ታርዤ
ልፋታቸውን ናውዤ
ከበሉት በልቼ
ከተኙት ተኝቼ
ኑሯቸውን ስኖር
በቀያቸው አፈር
ሞታቸውን ልሞት
ዕምነቴን ሳፀና
እግሬ በእግር ብረት
እጄ በካቴና
ተጠፍረው ታስረው
በእጅና በእግር አሙቅ
እስር ቤት  ስማቅቅ
ዘብጥያ ወርጄ
ጉልበት ስቸር ለህዝብ አቅም
እኔ ለእኔ ኑሬ አላውቅም።

ነሃሴ 2003
abraham beyenne

EthioLion.Com